# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## ፪ኛ ሰንበት (እሑድ)፥ ከመስከረም ፱ እስከ ፲፭ ቀን እሑድ ቢውል)

ከመስከረም ፱ እስከ ፲፭ ቀን ድረስ የፍሬ ዘመን ይባላል። በእነዚህ ዕለታት የሚዘመረው ያሬዳዊ መዝሙርም ሆነ የሚነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር ለምድር ፍሬን ለዘሪ ዘርን የሚሰጥ የዓለም መጋቢ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው።

### የዕለቱ ምስባክ

ምድርኒ ትሁብ ፍሬሃ
ወይባርከነ እግዚአብሔር አምላክነ
ወይባርከነ እግዚአብሔር

ምድር ፍሬዋን ትሰጣለች
እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል።
እግዚአብሔር ይባርከናል

መዝ ፷፮፥፮፯

ወንጌል፥ ማር ፬፥፳፮-፴፪
ቅዳሴ፥ ዘወልደ ነጐድጓድ (ጎቤክ)

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

እኩተ አንተ
«አንተ ምስጉን ነህ»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፪ኛ ቆሮ ፱፥፮-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፭፥፯-፲ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፬፥፳፩-ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### የዳነችና በምሕረትህ የጠገበች ነፍስ ታመሰግንሃለች።

ወቅቱ ዘመነ ፍሬ በመሆኑ የእግዚአብሔርን መግቦት በማሰብ የዕለቱን ትምህርት እንማራለን። ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ *«ዕኩት አንተ ወስቡሕ ስምከ ወዐቢይ ኃይልከ ዘተአርፍ በአርያም ወትሴባሕ በትሑታን ዘአንተ ሠራዕከ ሰንበተ ወጻድቅ መኑ ከማከ ዘታርሁ ክረምተ በጸጋከ ነፍስ ድኅንት ወነፍስ ርኅብት እንተ ፀግበት ተአኩተከ።»* ትርጉም፥ «አንተ ምስጉን ስምህም የተመሰገነ ኃይልህ ታላቅ በአርያም የምትኖር በትሑታን የምትመሰገን አንተ ነህ። ሰንበትን ለእረፍት የሠራህ ለሁሉም በእውነት ምግብን የምትሰጠው አቤቱ የምድርህን ፍሬ ባርክ ጻድቅና መሃሪ አምላክ ሆይ እንደ አንተ ያለ ማን ነው? ክረምትን በጸጋህ ታፈራርቃለህ፤ የዳነች ነፍስ በልታም የጠገበች የተራበች ነፍስ አንተን ታመሰግናለች።» በማለት የእግዚአብሔርን መጋቢነት ለምድር ፍሬን የሚሰጥ ለተራቡት እንጀራን የሚመግብ ክረምትና በጋን የሚያፈራርቅ መሆኑን እያሰበ እንዳመሰገነ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን በያሬዳዊ መዝሙሯ፤ በዳነ ሕይወትዋ የእግዚአብሔርን መጋቢነት እያስታወሰች ታመሰግናለች።



በአንደኛው ዲያቆን የተነበበው መልእክትም እግዚአብሔር ለዘሪ ዘሩን እንደሚሰጥ እንጀራም ከእርሱ እንደሆነ እያስታወሰ እኛም እግዚአብሔር ከሰጠን በረከት ቤተ ክርስቲያንን እንድንረዳ እንዲህ በማለት ያስተምረናል። « … በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፤ በበረከት የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ የሚዘጥ እርሱ የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል፤ ያበረክትላችሁማል። የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል።» (፪ኛ ቆሮ ፱፥፮-፲፪)። ይህ ክፍለ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን ለሌላም

የዳነችና በምሕረትህ የጠገበች ...

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

፪ኛ ሰንበት (እሑድ)፥ ከመስከረም ፱ እስከ ፲፭ ቀን እሑድ ቢውል)

እንድናካፍል የሚገልጽ እና እውነተኛው መግቦት ከላይ መሆኑን የሚያስተምር ነው። በሁለተኛው ዲያቆን የተነበበው መልእክትም በአንቀጸ ምጽዋት ላይ የተመሰረተ ሲሆን የእግዚአብሔርን መግቦትም የሚያስታውስ ነው። « ... እነሆ ገበሬው የፊተኛውን የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እያስታገሰ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠባበቃል፤ እናንተም ደግሞ ታገሱ ልባችሁንም አጽኑ።» (ያዕ ፭፤፯-፰)።

የተሰበከው ምስባክም ምድር ፍሬዋን ለሰዎች እንደምትሰጥ እግዚአብሔርም እየመገበ እንደሚባርከን የሚያስገነዝብ መሆኑን ወደኋላ አይተናል። የዕለቱ ወንጌልም ላይ ከቁጥር ፳፮ እስከ ፴፪ ያለው ቃል ወርኃ ፍሬን የሚያስታውስ የእግዚአብሔርን መጋቢነት የሚተረጉም ነው። በዚህ ክፍል ገበሬው ይዘራ እንጂ የሚያበቅል እግዚአብሔር፣ የሚያሳድግ እግዚአብሔር፣ የሚያሸት፣ ለፍሬም የሚያበቃ እግዚአብሔር እንደሆነ አብራርቷል።

አንባቢ ሆይ፥ ለምድር ፍሬን የሚሰጥ ዘመኑን በፍሬ ያስጌጠ የፍሬ ዘመንን ያዘጋጀ የተራበችን ነፍስ ዘወትር የሚመግብ ለገበሬ ዘርን ለምድር ፍሬን የሚሰጥ እንጀራን ከምድር የሚያበቅል መጋቢ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የፈጠረውንም ፍጥረት ሁል ጊዜ እንደሚመግበው እያሰብክ *(ነፍስ ድኅነት ወነፍስ ርህብት እንተ ፀግበት ተአኩተከ)* የዳነች ነፍስ ተርባ የጠገበች ነፍስ አንተን ታመሰግናለች እያልክ ከአባትህ ከቅዱስ ያሬድ ጋር ዘምር።

ጥቅስ በግእዝ፥ *ትጸውር ኩሎ እንዘ ኢትደክም ትሲሒ ለኩሉ እንዘ ኢተሐፅፅ ትሔሊ ለኩሉ እንዘ ኢታረምም።*
ትርጉም፥ ሳትደክም ሁሉን ትሸከማለህ፣ ሳትጐድል ለሁሉ ትመግባለህ፣ ዝም ሳትል ለሁሉ ታስባለህ። (ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቁ. ፪፻፶፩)



*ወበእንተ ፍሬ ማዕረር ዘአክሊለ ዓመት ከመ ትባርክ በምኅረትከ።*
«በየዓመቱ ስለሚያፈራው ስለመከሩ ፍሬ በምሕረትህ ይባረክ ዘንድ እንለምንሃለን።»
(ዝኒ ከማሁ ቁ. ፳፱)

ከላይ የተጠቀሱት የቅዳሴ ጥቅሶች እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ እንደ መዝሙሩ ሁሉ ዘመነ ፍሬን የሚያሳዩ፣ ወርኃ ፍሬን የሚሰብኩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በየወቅቱ እግዚአብሔርን እንዴት እንደምታመሰግን እያሰብን እኛም የአባቶቻችን ልጆች እንሆን ዘንድ በምስጋና እንትጋ።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር ... አሜን።